ፖለቲካ

# የመንግስት ጸጥታ ኃይሎች በመራዊ "ለፋኖ ድጋፍ አድርጋችኋል" በሚል ቢያንስ 45 ንጹሃንን ገድለዋል - ኢሰመኮ

"የፋኖ አባላት ናቸው" በሚል ተጠርጥረው የተያዙና ለጊዜው ብዛታቸውን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሰዎች በተመሳሳይ በመንግስት የጸጥታ ኃይሎች መገደላቸውንም ኮሚሽኑ ገልጿል

አል-ዐይን

2024/2/13 9:08 GMT

ይህ ድረገጽ የፍለጋ ልምድን ለማሻሻል ኩኪዎችን ይጠቀማል የግል ነፃነት አስማማለሁ



# በሸበል በረንታ እና ቋሪት ወረዳዎችም ከ21 በላይ ሲቪሎች በጸጥታ ሃይሎች መገደላቸው በኮሚሽኑ መግለጫ ተጠቅሷል

በሰሜን ጎጃም ዞን መራዊ ከተማ በርካታ ንጹሃን በመንግስት የጸጥታ ሃይሎች መገደላቸውን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት

ይህ ድረገጽ የፍለጋ ልምድን ለማሻሻል ኩኪዎችን ይጠቀማል   የግል ነፃነት

ኮሚሽኑ በሲቪል ሰዎች ላይ ስለደረሰው ጉዳት ምርመራ እያከናወነ ቢሆንም፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ምላሽ ያልሰጡ በመሆኑ፣ በጸጥታው ሁኔታና ልዩ ልዩ ተዛማጅ ምክንያቶች ሙሉ መረጃዎች ገና በተሟላ ሁኔታ ማሰባሰብ ባለመቻሉ የምርመራ ስራው በተሟላ መልኩ ሊጠናቀቅ አለመቻሉን ጠቅሷል፡፡

- የአማራ ክልል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መራዘሙ እንደሚያሳስበው ኢሰመኮ ገለጸ

ኢሰመኮ እስካሁን ድረስ ባደረገው ክትትልም የመንግሥት ጸጥታ ኃይሎች ማንነታቸውን ማረጋገጥ የቻላቸውን ቢያንስ 45 ሲቪል ሰዎች "ለፋኖ ድጋፍ አድርጋችኋል" በሚል ከህግ ውጭ መግደላቸውን ነው የገለጸው፡፡

ኮሚሽኑ ከደረሱት በርካታ ጥቆማዎችና ከልዩ ልዩ መረጃ ምንጮች ከተሰበሰቡት የሲቪል ሰዎች ስም ዝርዝር ውስጥ እስካሁን ድረስ ማንነታቸውን በመለየት ለማረጋገጥ የተቻለው 45 ሲቪል ሰዎችን ብቻ ቢሆንም የጉዳቱ መጠን ከዚህ ሊበልጥ እንደሚችል ምክንያታዊ ግምት መውሰድ ተችሏልም ነው ያለው፡፡

ከዚህም ባሻገር "የፋኖ አባላት ናቸው" በሚል ተጠርጥረው የተያዙና ለጊዜው ብዛታቸውን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሰዎች በተመሳሳይ በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ከህግ ውጭ መገደላቸውን ጠቁሟል፡፡

ለቀን ሥራ በጠዋት ከቤታቸው ወጥተው ድንገት ተኩስ ሲከፈት በአንድ ቦታ ተጠልለው የነበሩ 18 ሲቪል ሰዎች

ይህ ድረገጽ የፍለጋ ልምድን ለማሻሻል ኩኪዎችን ይጠቀማል የግል ነፃነት

በሌላ በኩል በምሥራቅ ጎጃም ዞን ሸበል በረንታ ወረዳ የዕድውኃ ከተማ 15 ሲቪሎች (ሴቶችን) ጨምሮ፤ በምዕራብ ጎጃም ዞን፤ ቋሪት ወረዳ ደግሞ 6 ሲቪል ሰዎች በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ከሕግ ውጭ መገደላቸውን ምስክሮች ለኢሰመኮ ማስረዳታቸው በመግለጫው ላይ ተጠቅሷል፡፡

የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ በአማራ ክልል በቀጠለው ግጭት በሲቪል ሰዎች ላይ እየደረሰ ያለው ስቃይ እጅግ እየጨመረ መምጣቱን በመጥቀስ ከሕግ ውጭ የሚፈጸም ግድያ ሙሉ በሙሉ እንዲቆምና ለዘላቂ መፍትሄ ሁሉም ወገኖች ሰላማዊ ውይይትን በቁርጠኝነት እንዲቀበሉ ጠይቀዋል፡፡

ኮሚሽኑ የተሟላ ምርመራ ተደርጎ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥና የተበደሉም እንዲካሱ አሁንም በድጋሚ ጥሪውን ያቀርባል ነው ያሉት፡፡

ኢትዮጵያ መነሻ ገጽ

#አነጋጋሪ_ጉዳዮች #አማራ

## ተዛማጅ ወሬ >

ይህ ድረገጽ የፍለጋ ልምድን ለማሻሻል ኩኪዎችን ይጠቀማል የግል ነፃነት